# እንዲህ ብለው ነበር

ክፍል:2  (ቅንብር አሥራደው ከፈረንሳይ)




I. « በሚገባ አውቃለሁ :: የኤሮፓ መንግሥታት አንድ አገር ለመያዝ ሲፈልጉ መጀመሪያ ሚስዮናውያንን ይልካሉ :: ቀጥለውም ሚስዮናውያኖቹን የሚያጠናክር ቆንሲል ብለው ይሾማሉ :: ከዚያም በኋላ ቆንሲሉን የሚጠብቅ ብለው የጦር ወታደሮችን ይልካሉ :: እኔ እንደ ሂንዱስታን ራጃ ቂል ሆኜ እንደዚያ እንዲደረግ የምፈቅድ አይደለሁም... »

አጤ ቴዎድሮስ

**አጤ ቴዎድሮስ** ከሚለው የጳውሎስ ኞኞ መጽሐፍ የተቀነጨበ ::

II. « የኔ ሴትነትና ያንተ ወንድነት የሚለካው እዚያው ጦር ሜዳ ነውና እንዳትቀር ! »

**እተጌ ጣይቱ ብጡል**

የጣሊያን መልክተኛ የነበረው ኮንት አንቶኔሊ በ1883 « አፄ ምኒልክ መንግሥታዊ ስልጣኑን ለአንዲት ሴት ለቆ ይጫወትብኛል » ብሎ ያወራ ስለነበር ይህ ወሬ ለእተጌ ጣይቱ በመድረሱ የሰጡት መልስ ነበር ::

**ጣይቱ ብጡል** ከሚለው ከቀኛዝማች ታደሰ ዘውዴ መጽሐፍ የተወሰደ ::

III. « ምናምንቴውንና ጥርቃሞውን እየመለመሉ ወታረርና ሰላይ በማድረግ ሕዝቡን የርስ በርስ እምነት አሳጥተውታል ::
ጠላት ከሚሠራው ግፍና የእብሪት ሥራ ይልቅ ሆድ የሚያቃጥለው ያንዳንድ የኛው ሰው ሁኔታ ነው :: በተፈጥሯቸው ደካማነትና ለገንዘብ በመስገብገባቸው ለክብራቸውና ላገራቸው ምንም ፍቅር የሌላቸው ሆነው የሚያደርጉት ሥራና የሚያሳዩት ሁኔታ የሚያሳዝን ነው:: ይህ የፈተና ሰዓት ሰንቱን ወርቅ ይመስል የነበረውን ነሐስ አደረገው፤ ብር ይመስል የነበረውን ቆርቆሮ አደረገው :: »

ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት

በአምስቱ ዓመት የጣሊያን ወረራ ዘመን የነበረውን ሁኔታ ሲገልጹ ::
ደጃዝማች ያሁኑን ቢያዩ ምንኛ ባዘኑ !!

**አርአያ** ከሚለው ቁምነገር አዘል መጽሐፋቸው የተወሰደ ::